# የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን

## የ2017 በጀት አመት ዕቅድ

Bosena

ኢግባ

ሰኔ 2016

ማውጫ ገጽ


1. መግቢያ ........ 4

1.1 የእቅዱ አስፈላጊነት ........ 4

1.2 የእቅዱ መነሻ ........ 4

1.3 የባለሰለጣኑ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶቸ ........ 5

1.3 የባለስልጣኑ ስትራቴጅክ ግቦችና /ቁልፍ ተግባራት በፕሮግራሞች ........ 6

1.4 የሁኔታዎች ትንተና (SWOT Analysis) ........ 7

የነበሩ ጠንካራ ጎኖች ........ 7

መልካም አጋጣሚዎች ........ 7

ስጋቶች ........ 8

2. የ2016 በጀት አመት የዕቅድ አፈጻጸም ........ 8

3. የ2017 በጀት አመት ዕቅድ ........ 8

3.1 የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቁጥጥር ማጠናከር ........ 9

3.1.1 ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ........ 9

ለ ........ 9

3.1.2 በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ........ 9

3.2 የእጽዋት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር ........ 10

3.2.1 ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ እና የአፈር ማዳበሪያ ........ 10

3.2.1.2 ጥራቱ የተረጋገጠ የአፈር ማዳበሪያ ........ 10

3.2.2 ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች ........ 12

3.2.2.1 ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች ........ 12

ለ 87531 ሜትሪክ ቶን የዕፅዋት ዉጤቶች ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ እንዲላክ ይረጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ........ 12

3.2.2.2 ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች ........ 13

3.2.2.4 የእፀዋት ዝርያ ጥበቃና ዘር ጥራት ቁጥጥር ........ 13

በምርምር ቀርበው የተገመገሙ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎች ........ 13

3.2.2.5 ደረጃውን የጠበቀ የእፀዋት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት ........ 14

3.2 የእንስሳት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር 15
3.3.1 የእንሰሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ 15
3.2.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች 16
3.2.3 ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት 17
3.2.4 ጥራትና ደህነነቱ የተረጋገጠ የእንሰሳት መኖ 17
3.3.4.1 የመኖ ተቋማትና ባለሙያዎች የተሰጠ የብቃት ማረጋገጥ 17
3.3.4.2 ጥራትና ደህንነቱ ተጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ መኖ እና የመኖ ግብዓት 18
3.3.4.3 የእንሳሰት መኖ እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ማካሄድ 18
3.2.5 ደረጃውን የጠበቀ የእንሰሳት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት 19
4 ተቋማዊ የመፈፀም አቅም፣ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምና አገልግሎት አሰጣጥ እና የህግ ማዕቀፎች 20
4.1 የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር 20
4.2 ተግባራዊ የተደረገ የህግ ማዕቀፍ 20
4.3 የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ሪፖርት ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ-መልስን ማሻሻል 21
4.4 የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል 21
4.5 የፋይናንስና ግዥና አስተዳደር 21
4.6 መሰረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት የደንበኞችን እርካታ ማሻሻል 21
4.7 የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ለውጤታማነትን ማሻሻል 21
4.8 ተቋማዊ የሪፎርም ሥርዓት በመጠቀም የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ 22
4.9 አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት 22
በ2016 ከተደረገው ጥረት በላቀ ሁኔታ ተጠናክሮና ተሻሽሎ ይቀጥላል፡፡ 22
4.10 ክትትልና ግምገማ 22
ማጠቃለያ /ቀጣይና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች 22

**ደርሞ**

*የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የግብርና ምርቶችን፣ግብዓቶችንና ፣ አገልግሎቶችንና የግብርና ቴክኖሎጂ፣ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቁጥጥር ስራዎችን እንዲያከናውን ስልጣን የተሰጠው የግብርና ቁጥጥር ተቋም ነው፡፡ባለስልጣኑ በሁለት ዋና ዋና የቁጥጥር ፕሮግራሞች ማለትም በዕጽዋት ቁጥጥር ዘርፍ እንዲሁም በእንስሳት ቁጥጥር ስር ባሉ ክፍሎቹ የተደራጀና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚሄድ የቁጥጥር ተግባትን እያከናወነ ሲሆን ከነዚህ ዘርፎች በተጨማሪም የግብርና ሜካናይዜሽን ፣ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ቁጥጥር ስራ ለማስጀመር እየሠራ ይገኛል ፡፡ ይህ የዕቅድ ሰነድ በተለይም የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ መሠረት ባደረጉ የቁልፍ ተግባራት አመልካቾች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ ዕቅድ የአጠቃላይ የግብርና ሴክተር ዕቅድ አካል ሲሆን ወቅቱን የዋጀ የክትትልና ግምገማ ስርዓትን በመከተል እንዲሁም ከሁሉም ባለድርሻና ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት የሚከናወን ይሆናል፡፡*

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በ2021 በፌዴራል ፓርላማ በአዋጅ ቁጥር 1263/2021 አንቀጽ 11 ላይ በመመስረት ስልጣኑ እና ሚናው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 509/2022 ተለይቷል። ባለስልጣኑ በዋናነት የቁጥጥር ተግባራት መሠረት በማድረግ በዋና ዋና ምርቶችና አገልግሎቶች ማለትም የግብርና ቴክኖሎጂዎች፣ የግብርና ግብአቶች፣ የግብርና ምርቶች እና የግብርና አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ፣ የተመዘገቡ እና የምስክር ወረቀት ብቃት ባለው ሰው የሚመሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። የግብርና ምርቶች እና አገልግሎቶች የአፈጻጸም/ውጤታማነት፣ የጥራት፣ የጤና እና የደህንነት ደረጃዎችን የሚያከብሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተከታታይ ምርመራዎችን ያደርጋል እንደ አስፈላጊነቱ የቁጥጥር እርምጃዎችን ይወስዳል።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ10 ዓመትና የመካከለኛ ዘመን የግብርና ሴክተር ዕቅድ አካል የሆነውን የግብርና ሬጉላቶሪ ዕቅድ መሠረት በማድረግ የ2017 ዓመታዊ ዕቅድ ዝግጅት ስራ አጠናቋል። በዕቅድ ዝግጅቱ ወቅት ታሳቢ ከተደረጉ ጉዳዮች መካከል በ2016 የተገኙ ተሞክሮዎች ዋናውን ድርሻ  የያዙ ሲሆን ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችም ታሳቢ ተደርገዋል። የተጀመሩ ቅንጅታዊ አሠራሮች እንዲሁም ወሳኝ የሆኑና ለቁጥጥሩ ጥራትና ቅልጥፍና እገዛ የሚያደርጉ፣ በስትራቴጂክ ዕቅዱም በዋናና ልዩ የትኩረት መስክነት የተያዙ፣ እንደ ዲጂታይዜሽን ፣የህግ ማዕቀፍ ማሻሻያ ስራዎችን ታሳቢ ያደረገና ባለው የሰው ሀይልና ሌሎች ሀብቶች ተጠቅሞ ሊደረስበት የሚችል ዕቅድ አዘጋጅቶ አቅርቧል።

### 1.1 የእቅዱ አስፈላጊነት

እንደ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን በየጊዜው ሊለካ የሚችል ግብ በማስቀመጥ በ10 አመት እንደርስበታለን ብለን ያቀድነው ግብ ላይ ለመድረስ በየአመቱ እቅዳችን ሊራመድ የሚችልና አሳታፊ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል ይህንንም መነሻ በማድረግ በአመቱ ስኬታማ ሊሆን የሚችል ፣ሊለካ የሚችል እንዲሁም በምን ያህል መጠን ይሳካል? የሚለውን በየጊዜው ለመከታተል ያመች ዘንድ ይህ አመታዊ እቅድ ማዘጋጀት አስፈልጓል።

### 1.2 የእቅዱ መነሻ

ዕቅዱን ዉጤታማ ለማድረግ ከዚህ በፊት ያጋጠሙ ችግሮች እና መልካም እድሎችን በሚገባ መመርመርና እንደ ግብረመልስ ተጠቅሞ ለዕቅድ መነሻ ማድረግ በጣም ጠቃሚ መሆኑ ይታመናል። በዚህ መሠረት የ2017 በጀት አመት የግብርና ባለስልጣን እቅድ እንደመነሻ አድርጉ የያዘው

- የግብርና ሚኒስቴር የ10 አመት እና የመካከለኛ ዘመን እቅድ
- የባለስለጣኑ የ10 አመት እና የመካከለኛ ዘመን እቅድ
- የባለስልጣኑን የ2016 በጀት አመት አፈጻጸም
- በተለያየ ደረጃ የተደረጉ ግምገማዎችና የተሰጡ ግብረ መልሶቸ

- ባለስልጣኑ አሁን ባለበት ደረጃ ያለውን የሰውና ሌሎች ሀብቶች እንደ መነሻ ለመጠቀም ተችሏል፡፡

## 1.3 የባለሰለጣኑ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶቸ

**ተልዕኮ**

የግብርና ቴክኖሎጂ፣አገልግሎቶችን ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ደህንነት፣ፍቱንነት፣ ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤መልካም ስም ያለውና ፣ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓትን በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የግብርና ምርቶችን የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኤኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት፡፡

**ራዕይ**

በአለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም መሆን

**እሴቶች**

Loyalty ታማኝነት

- Confidentiality/ሚስጥር ጠባቂነት
- Commitment አገልጋይነት
- Rule of the law /የህግ የበላይነት
- Accountability /ተጠያቂነት

•Customer focus ደንበኛ ተኮር አገልግሎት

- Impartiality /አለማዳላት
- Partnership /ትብብር
- Transparency. /ግልጽነት
- Responsiveness /ምላሽ ሰጪነት

## 1.3 የባለስልጣኑ ስትራቴጂክ ግቦችና /ቁልፍ ተግባራት በፕሮግራሞች

**ውጤታማነት፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ**

- ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ
- በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

**የእፀዋት በዕጽዋትና ፣ከእፀዋት ጋር በተገናኙ ግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ማጠናከር**

- ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ
- ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች
- የዕጽዋት ዝርያ ጥበቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር
- ደረጃውን የጠበቀ የእፀዋት ጥራት ምርመራ ላብራቶነሪ አገልግሎት

**የእንስሳትና ከእንስሳት ጋር የተገናኙ የግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ቁጥጥር ማጠናከር**

- የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ
- በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች
- ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት
- ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ
- ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት

**ተቋማዊ የመፈፀም አቅም ግንባታ፣ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምና አገልግሎት አሰጣጥ እና የህግ ማዕቀፎች**

- የአቅም ግንባታ ሥራዎች
- የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት ማሻሻል
- የሃብት አጠቃቀምን ማሳደግ እና ሃብት ማፈላለግ
- የእቅድ ክትልና ግብረ መልስ ሥራዎችን ማከናወን
- ተቋማዊ አገልግሎትን ማሻሻል
- ሥርዓተ ጾታና ማህበራዊ አገልግሎት መተግበር
- ተቋማዊ ዲጅተላይ"ዘሽን አገልግሎት መስጠት
- ተቋማዊ ሪፎርም አተገባበር
- አጋርነት እና ህዝብ ግንኙት
- ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና

## 1.4 የሁኔታዎች ትንተና (SWOT Analysis)

**የነበሩ ጠንካራ ጎኖች**

- በስራ ላይ ያለውን የሰው ሀይል በስራ ቦታው ላይ መድቦ ማሰራት መቻሉ፣
- የእንስሳት ግብአት እና የምርት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ መኖር፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ የተፈቀዱ ህጎች፣ የፕሮቶኮሎች ደረጃዎች፣ ቴክኒካዊ መመሪያዎች በተወሰኑ ቁጥጥር ስር ባሉ ግብአቶች እና ምርቶች ውስጥ መኖር
- ወደ ዲጅታላይዜሽን አሠራር ሥርዓት የተሸጋገሩ የምዝገባና ሰርትፊኬት አሰጣጥ ሥርዓቶች ጅምር መኖር ፣
- የተለያዩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ስልጠናዎች መሰጠታቸው፣
- የቡድን ሥራን ለማሳለጥ የተሰጡ የተለያዩ የሥልጠናና የአቅም ግምባታ ስራዎች መከናወናቸው፣
- የቁጥር ስራዎን ለማዘመንና ተደራሽ ለማድረግ አመራር ቁርጠኝነት መኖሩ፣
- መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ ተቀናጅቶ መስራት መቻሉ፣
- ፖሊሲዎችን፣ አዋጅ፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን በማዘጋጀት የተወሰኑት በመጽደቅ ሂደት ላይ ቢሆኑም የፀደቁትን ለሚመለከታቸው አካላት የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱ፣

**ደካማ ጐኖች**

- በተወሰኑ የግብርና ቴክኖሎጂዎች፣ አገልግሎቶች፣ ግብዓቶች እና ምርቶች ላይ የተጠናከረና የጸደቀ የህግ ማዕቀፍ አለመኖርና የማጽደቅ ሂደቱ መርዘም
- ተቀባይነት ያለው የዕጽዋትና የእንስሳት ሬጉላቶሪ ስራ ለመስራት የሚያስችል የሰው ሀይልና ሎጅስቲክ አቅም ክፍተት በፌደራልም ሆነ በማዕከል ደረጃ መኖር.
- የዕፅዋት ግብዓት እና ምርት ምርመራ ላቦራቶሪውን አቅም በመገንባት እውቅናና ተቀባይነት ያለው የምርመራ ማዕከል ለማድረግና የክልል ላቦራቶሪዎች የጥራት ፍተሻ አቅም ለመገምገም የሚያስችል ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያገኘ (Accredidated) ላቦራቶሪ ያለመኖሩ.
- በድህረ ጥራት ፍተሻ ጣቢያዎች የቁጥጥር ስራቸውን በስታንዳርዱ መሰረት ለመስራት የሚያስችል የቁሳቁስና የመሰረተ ልማት ክፍተት መኖሩ፡፡
- የሀብት እጥረት መኖር የሚሉት ይገኙበታል፡፡

**መልካም አጋጣሚዎች**

- መንግስት ለግብርና ግብዓት እና ምርቶች ጥራት ቁጥጥር በተሰጠው ትኩረት የኢትዮጰያ ግብርና ባለስልጣን መመስረቱ፣
- ከክልሎች ጋር በትብብር መስራት መቻሉ፣
- ሀገሪቱ በየደረጃው ከሀገራት ጋር የፈጠረቻቸው ዲፕሎማሲያዊና የትብብር ሁኔታዎች ለወጪ ንግድ ቁጥጥር አመቺ ሁኔታ መፍጠራቸው፣

**ስጋቶች**

- የተጠናከረ ላብራቶሪ ባለመኖሩ ከውጪ የሚገቡ የግብርና ግብዓት እና ምርቶችን ብቃት፣ ጥራት ፣ ደህንነት ፣ ፍቱንነት እና ጤንነት ለማረጋገጥ ተፈላጊው አቅም አለመግንባቱ.
- የግብርና ቴክኖሎጂ እና ግብዓት ብቃት እናፍቱንነት የሚፈተሽበት የሙከራ ቦታዎች ማግኘት አለመቻል፤
- ለቁጥጥር ተግባራት የሚያስፈልጉ የህግ ማዕቀፎች ፀድቀው ወደ ሥራ የሚገባበት በተለያዩ ምክንያቶች መርዘም፣
- ባለስልጣኑ የራሱ የሆነ ቢሮ አለመኖሩ/ ኪራይ መሆኑ/፣

## 2. የ2016 በጀት አመት የዕቅድ አፈጻጸም

የ2016 በጀት አመት የቁልፍ አመልካቾች የእቅድ ክንውን በዚህ ሪፖረት መጨረሻ ላየ ባለው ሰንጠረዥ ላይ ለ2017 እቅድ መነሻ ሆኖ ተመላክቷል።

## 3. የ2017 በጀት አመት ዕቅድ

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የአንድ ዕቅድ አንድ ሪፖርት አቀራረብ የሚከተል ሲሆን የአስር ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዱን መሠረት በማድረግ የሚከናወኑና በ4 ፕሮግራሞች ፣በ9 ስትራቴጂክ አላማዎች እንዲሁም እነዚህን ስትራቴጂክ አላማዎች ለማሳካት በሚከናወኑ ቁልፍ አመልካቾች የተመሠረተ ነው ።ይህንን መሠረት አድርጎም የባለስልጣኑ የ2017 ዕቅድ በፕሮግራሞች በስትራቴጂክ አላማዎች እንዲሁም በቁልፍ አመልካቾ ላይ መሠረት ያደረገ ዕቅድ እንደሚከተለው ቀረቧል።

### 3.1 የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቁጥጥር ማጠናከር

#### 3.1.1 ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ

ለ 20 የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ተቋማት ውጤታማታቸው ፣የጥራትና ተስማሚነቱ ሁኔታቸውን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዷል፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞም ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

- 20 የግብርና ማሽነሪዎችን መመዝገብ እና ዕውቅና መስጠት፣
- 10 የግብርና ማሽነሪዎችን የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ መስጠት፣
- 20 የግብርና ማሽነሪዎችን በመግቢያና መውጫ ኬላ የመልቀቂያ ፈቃድ መስጠት፣
- 10 በመግቢያና መውጫ ኬላ በፍተሻ ለማረጋገጥ ናሙና መውሰድ፣
- 20 የግብርና ማሽነሪዎችን ጥራት በሰነድ ግምገማ ማረጋገጥ፣
- 2 የግብርና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች/ቴክኖሎጂዎች በመገምገም የሙከራ ፈቃድ መስጠት፣
- 2 የግብርና ምርምር ቴክኖሎጂዎችን የሙከራ ምርምር እንዲካሄድባቸው ፈቃድ መስጠትና መመዝገብ፣
- 24 የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ባለሙያዎችን መመዝገብና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መስጠት፣

#### 3.1.2 በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

ለ 30 የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብቃታቸውን የማረጋገጥና ስራ ይከናወናል፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞም ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

- ለ10 ግብርና ማሽነሪ አስመጪዎች ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
- ለ5 ግብርና ማሽነሪ አምራች ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
- 3 የግብርና ምርምር ተቋማትን መመዝገብና የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
- 4 የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን መመዝገብና ዕውቅና ይሰጣል፡፡
- 12 ለግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
- 10 በግብርና ማሽነሪዎች አስመጪዎች ድንገተኛ የኢንስፔክሽን ፍተሻ ይካሄዳል፡፡
- 5 በግብርና ማሽነሪዎች አምራቾች ድንገተኛ የኢንስፔክሽን ፍተሻ ይካሄዳል፡
- 10 በግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪዎች ድንገተኛ የኢንስፔክሽን ፍተሻ ይካሄዳል፡
- በ5 በግብርና ኤክስቴንሽን ተቋማት ላይ ድንገተኛ የኢንስፔክሽን ፍተሻ ይካሄዳል፡፡

## 3.2 የእጽዋት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር

### 3.2.1 ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ እና  የአፈር ማዳበሪያ

ለ 111437 ሜትሪክ ቶን ፀረ ተባይ ፍቱንነትና ፣ደህንነትንና ጥራትን የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞም ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

#### 3.2.1.1 ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ

ለ230 የቅድመ የማስገቢያ ፈቃድ ጥያቄዎችን በመገምገም መስፈርቱት ሲያሟሉ ፍቃዱን መስጠት፣ለ111437 ሚትሪክ ቶን ፀረ ተባይ የመግቢያ ፍቃድ ይሰጣል ፡፡

- ✓ 225 የመስክ ውጤታማነት ሙከራ ጥያቄ ሰነድ መገምገምና ፈቃድ የመስጠት ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ መስፈርቶችን ያሟሉ 275 ዶሴሮችን (dossier) የመረከብ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ 245 ዶሴሮችን(dossier) የባለሞያዎች የቴክኒክ ግምገማ ይከናወናል፡፡
- ✓ የቴክኒክ ግምገማውን ላለፉ 235 ፀረ-ተባይ ሰርተፊኬት የማዘጋጀት እና የመስጠት ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ የ8 ምዝገባ ዝርዝር ወቅታዊ ማድረግ እና ተደራሽ ይደረጋል፡፡
- ✓ 130 የምዝገባ ዕድሳት እና ማሻሻል ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ የፍቱንነት ወይም የይዘት ሙከራ በሚሰሩ ቤተሙከራዎች አና የምርምር ማዕከላት 4ጊዜ ኢንስፔክሽን ይከናወናል፡፡

#### 3.2.1.2 ጥራቱ የተረጋገጠ የአፈር ማዳበሪያ

ለ 2,339,971 ሜትሪክ ቶን ማዳበሪያ ጥራቱ የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም

- ✓ 600 የቅድመ የማስገቢያ ፈቃድ ጥያቄዎችን በመገምገም መስፈርቱት ሲያሟሉ ፍቃዱን ይሰጣል፡፡
- ✓ ለ2,651,118 ቶን የአፈር ማዳበሪያ የመግቢያ ፍቃድ ይሰጣል፡፡
- ✓ 20 የመስክ ውጤታማነትን ሙከራ ጥያቄ ሰነድ መገምገምና ፍቃድ መስጠት
- ✓ መስፈርቶችን ያሟሉ 20 ዶሴሮችን (dossier) መረከብ
- ✓ 20 ዶሴሮች (dossier) የባለሙያወች የቴክኒክ ግምገማ ይከናወናል፡፡
- ✓ የቴክኒክ ግምገማውን ላለፉ 20 የአፈር ማዳበሪያዎች ሰርተፊኬት የማዘጋጀት እና የመስጠት ሰራ ይከናወናል፡፡
- ✓ 4 ጊዜ የምዝገባ ዝርዝር ወቅታዊ ይደረጋል፡፡
- ✓ 30 የምዝገባ ዕድሳተ እና ማሻሻል ሥራ ይከናወናል፡፡

#### 3.2.1.3 በአካባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶች በጥናት መቀነስ

በአካባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶች በጥናት ስለመቀነስ የ2 ሰነድ ዝግጅት ይከናወናል፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞም

- ✓ ከፀረ-ተባይ አጠቃቀም ጋር ያሉ ስጋቶችን አስመልክቶ ጥናት ይደረጋል፡፡
- ✓ የማዳበሪያ አጠቃቀም ጋር ያሉ ስጋቶችን አስመልክቶ ጥናት ይደረጋል፡፡
- ✓ የፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ የድህረ-ምዝገባ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ የምክረ-ሀሳብ ሰነዶችን ይዘጋጃል፡፡
- ✓ የፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ የድህረ-ምዝገባ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ የምክረ-ሀሳብ ሰነዶችን ለባለድርሻ አካላት የማሳወቅ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ በሰው እና በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የፀረ ተባይ (highly hazardeous pesticide) መለየት የሚያስችል ጥናት ይደረጋል፡፡
- ✓ ጊዜ ያለፈበት ፀረ ተባይ/Obsolate pesticide/ላይ ዳሰሳ ጥናትና መረጃ የመሰብሰብ ስራ ይከናወናል፡፡

**3.2.1.4 የብቅት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች /195/**

ለ 195 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

- ✓ ለ60 አዳዲስ ተቋማት በምዝገባ መስፈርቱ መሰረት የመመዝገብ እና የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
- ✓ ለ135 ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ የማደስ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ ለ8 የፀረ ተባይ እና አፈር ማዳበሪያ ተቋማት ዝርዝር ወቅታዊ እና ተደራሽ የማድረግ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ ለ 4 የፀረ ተባይ እና ማዳበሪያ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ላይ ድንገተኛ ፍተሸ ይደረጋል፡፡
- ✓ የፍቱንነት ወይም የይዘት ሙከራ በሚሰሩ ቤተሙከራዎች እና የምርምር ማዕከላት 4 ጊዜ የኢንስፔክሽን ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ የተቋማት የፀረ-ተባይ ብቃት ማረጋገጫ አሰጠጥ ሥራ ይከናወናል፡፡

3.2.2 ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች

### 3.2.2.1 ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች

ለ 87531 ሜትሪክ ቶን የዕፅዋት ዉጤቶች ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ እንዲላክ ይረጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

- ✓ ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ በተመረጡ 300 የግብርና ምርቶች ላይ የማዕጠንት/Fumigation/ክትትል ይደረጋል፡፡
- ✓ ወደ ውጪ ለሚወጣ 50,000የዕፅዋት ምርት የጤንነት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ይሰጣል፡፡
- ✓ ወደ ውጭ የሚላኩ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች ተቀባይነታቸውን የማሳደግ እና የተቀባይ ሃገራትን ቅሬታ(Notification) የመቀነስ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡
- ✓ ለ56 የአበባ፣የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎችን በየሩብ ዓመቱ የመስክ ቁጥጥርና ክትትል የማድረግና ሞያዊ ድጋፍ የመስጠት ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ ወደ አውሮፓ ህብረት በሚላኩ የሮዝ አበባ ምርቶችን 8 ጊዜ ውጫዊ ኦዲት የማድረግ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ ለ44 የአበባ፣የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎችን በየሩብ ዓመቱ የመስክ ቁጥጥርና ክትትል የማድረግና ሞያዊ ድጋፍ የመስጠት ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ Xylella fastidiosa ጨምሮ ሌሎች የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት ተደርጎ በተመረጡ የዕፅዋት ተባዮች ላይ በመስክ ዳሰሳ እና ቅኝት በማካሄድ እንዲሁም በላብራቶሪ እንዲመረመር በማድረግ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የመላክ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ ለዕፅዋትና ዕፅዋት ዉጤቶች ተቀባይ ሀገር የተባይ ስጋት ትንተና ቴክኒካል መረጃ/ሰነድ የመላክ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ ለጥራጥሬ እና ቅባት እህሎች አበጣሪ እና አቀነባባሪእና ለቡና አበጣሪ እና ላኪ ድርጅቶች በምግብ ደህንነት አስተዳደር ስርዓት ላይ : ብሄራዊ እና አለምአቀፍ ደረጃዎች ላይ 4 ጊዜ ስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ይሰጣል፡፡
- ✓ የሰሊጥ አምራቾች በሳልሞኔላ ምክንያት ወደ አውሮፓ ኤክስፖርት መቀዛቀዝ እንዳይከሰት ተገቢ የሆነ የላብራቶሪ ምርመራ እንዲያካሂዱ የመከታተል ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በምግብ ደህንነት አስተዳደር ስርዓት ላይ፤ብሔራዊ የመከታተያ ሥርዓት (National traceability system) ወርክ ሾፕ ይካሄዳል፡፡
- ✓ በእፅዋት ምርት ጥራትና ደህንነት ከእርሻ እስከ ገበታ ለክልልና ከተማ አስተዳደር ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፡፡

### 3.2.2.2 ጤንነቱ፣ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች

ለ60000 ሜትሪክ ቶን የዕጽዋት ውጤቶች የጤንነትና ጥራት ማረጋገጫ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም

- ✓ የዕፅዋት ኳራንቲን ተባይ ወደ ሀገሪቱ ከመግባቱ በፊት መተንበይና ገብቶ ሲገኝ በአፋጣኝ የመቆጣጠሪያ ዘዴ በመጠቀም ተባዩ በአስቸኳይ እንዲጠፋ ክትትል ይደረጋል፡፡
- ✓ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ 2024 ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ዉጤቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች የሚገቡባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኂላ የጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ ይሰጣል፡፡
- ✓ በድህረ መግባት ኳራንቲን (Post Entry Quarantine) ማለፍ ያለባቸውን እፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች 6 ጊዜ ክትትል ይደረጋል፡፡
- ✓ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ 2,195 ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶችና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
- ✓ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ዕፅዋትና የዕፅዋት ዉጤቶች የተባይ ስጋት ትንተና የመስክ የዳሰሳ ጥናት ይካሄዳል፡፡
- ✓ ለዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች የጥራት እና ደህንነት የደረጃዎች ዝግጅት ይካሄዳል፡፡

### 3.2.2.3 የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች

ለ 230 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ቀጣዮቹ ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

- ✓ የዕፅዋት እና የዕፅዋት ውጤት ወደ ውጪ ሀገር ለመላክና ለማስመጣት እንዲሁም በማጥንት ሰራ ላይ ለተሰማሩ 200 አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች/ግለሰቦች አስፈላጊውን የቢሮና የመጋዘን ኢንስፔክሽን በማካሄድ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
- ✓ ከስራ ክፍሉ የብቃት ማረጋገጫ ስርተፊኬት ለተሰጣቸው 30 ተቋማት ተገቢውን የቢሮና የመጋዘን ኢንሰፔክሽን  በማድረግ ሰርተፊኬታቸውን የማደስ ስራ ይከናወናል፡፡
- ✓ በዕፅዋትና የግብርና ምርቶችን ስራ ብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ 36 ለንግድ የሚሰሩ ድርጅቶች /ግለሰቦች በመስፈርቱ መሰረት እየሰሩ ስለመሆናቸዉ ክትትልና ግምገማ ይደረጋል፡፡

3.2.2.4 የእፀዋት ዝርያ ጥበቃና ዘር ጥራት ቁጥጥር

**በምርምር ቀርበው የተገመገሙ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎች**

**ቁልፍ ተግባራት**

ለ120 በምርምር የቀረቡ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎችን ግምገማ ይካሄዳል። ከዚህ ጋር ተያይዞም ቀጣዮቹ ዝዝር ተግባራት ይከናወናሉ፡፤

- ✓ 78 የዕፅዋት ዝርያዎች ጥራትና ዉጤታማነታቸው ተረጋግጦ ይመዘገባሉ ይለቀቃሉ።
- ✓ 1,527,905 ኩ/ል የአገር ውስጥ ዘር በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱን የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል።
- ✓ በቁጥር 250 ከውጪ የገባ ዘር ናሙና ጥራቱ በላብራቶሪ እንዲፈተሽ ይደረጋል።
- ✓ 509,603 ኪሎግራም ከውጭ አገር ሚገባ ዘር በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ ይረጋገጣል።
- ✓ ለ30 ዘር ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል።

### 3.2.2.5 ደረጃውን የጠበቀ የእፀዋት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት

**የእፀዋት ላብራቶሪ አሰራር ስርአቶችን መዘርጋት**

- ✓ አንድ (1) ማእከል የሆነ የላቦራቶሪ ኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ሲስተም ፕሮግራም (LIMS/IT-Program)) አገልግሎትን ይጀምራል።
- ✓ የእጽዋት ግብአት ምርት ጥራትና ደህንነት ምርመራ የሚሰሩ ተቋማትን በመለየት ዕውቅና የሚሰጥበት አሰራርን ይዘረጋል።
- ✓ በክልሎችና በፌደራል ደረጃ ባሉ የዘር ጥራት ምርመራ ላብራቶሪዎች በአጠቃላይ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ሰነድ ይዘጋጃል።
- ✓ ለስድስት (6) የላብራቶሪ አናሊስቶች የላቦራቶሪ የሙያ ፈቃድ ይሰጣል።
- ✓ ለአራት (4) ላብራቶሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል።
- ✓ የጥራትና ደህንነት ፍተሻ/ምርመራ ስራ በሚሰሩ ቤተ-ሙከራዎች ላይ የኢንስፔክሽንና የኦዲት ስራ ይከናወናል።
- ✓ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ የእፅዋት ላቦራቶሪ የምርመራ መሳሪያዎች፣ የኬሚካል ግብአቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእፅዋት ላቦራቶሪ ቁሳቁሶች የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል።
- ✓ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ የእፅዋት ላቦራቶሪ የምርመራ መሳሪያዎች፣ የኬሚካል ግብአቶች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእፅዋት ላቦራቶሪ ቁሳቁሶች የሚገቡባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ የጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ ይሰጣል።

**የተዘረጋ የእጽዋት የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ISTA-Accreditation and (ISO/IEC 17025)**

- ✓ የምርመራ ሥነ-ዘዴ ትክክለኛነት (Test Method Verification/validation) ማረጋገጫ ተግባራትን ማከናወን
- ✓ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ዓመታዊ ካሊብሬሽን ማከናወን
- ✓ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ጥገና ተግባራት ማከናወን
- ✓ የምርመራ ብቃት ማረጋገጫ (PT) በዘር ጥራት እና በምግብ ደህንነት ናሙናዎች ላይ ተሳትፎ ማሳደግ
- ✓ የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ የውስጥ ኦዲት ማከናወን
- ✓ የላቦራቶሪ መረጃ ስርዓት ማዘመንና የመረጃ አቅርቦትና አጠቃቀም ማሻሻል (የላቦራቶሪ ምርመራ እና ተያያዥ ቴክኒካል ሥራዎች መረጃ ማደራጀት)
- ✓ ቋሚ እና አላቂ የላቦራቶሪ የምርመራ መሳሪያዎችና ግብአቶች እንዲሁም የተለያዩ ተያያዥ ቁሳቁሶች መረጃዎችን በሰነድና ኤሌክትሮንክስ አማራጮች ማደራጀት
- ✓ አዲስ የሶስተኛ ወገን እውቅና ለሚጠየቅባቸው የምርመራ ስነ-ዘዴዎች እውቅና ለማግኘት የሚረዱ ሰነዶችን ማደረጀትና የሶስተኛ ወገን የእውቅና ጥያቄ ለብሔራዊ አክሪድቴሽን ጽ/ቤት ማቅረብ

**3.2 የእንስሳት ግብዓቶች ምርቶች እና አገልግሎት ቁጥጥር ማጠናከር**

**3.3.1 የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ**

**3.3.1.1 ጤንንነቱ ጥራቱና ደህንነቱ፣ ተረጋግጦ የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት በማሟላት ለወጪ ገቢያ ብቁ ሆኖ የቀረበ ሥጋና ተረፈ ሥጋ፣**

ወደ ውጭ ለሚላከ 15000 ቶን ስጋና ተረፈ ሥጋ ደህንነት ጥራትና ጤንነቱን የማረገጋጥ ስራ ይከናወናል፤

- ✓ በ ለ1,850,000 የቁም እንስሳት የቅድመ ዕርድ ምርመራ ይከናወናል፤
- ✓ ለ80000የድህረ ዕርድ ምርመራ ይከናወናል ::
- ✓ ለ15000 ቶን ሥጋና ተረፈ ሥጋ፣ ጤንንነቱ ጥራቱና ደህንነቱ፣ ተረጋግጦ የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት በሚሟላት ለወጪ ገቢያ ይቀርባል::
- ✓ ለስጋና ተረፈ ስጋ 7000 ዓለም ዓቀፍ የጤና ማረጋገጫ ሰርፊኬት ይሰጣል::
- ✓ 300 ጥራዝ ዓለም አቀፍ የጤና ሰርትፊኬት በማሳተም ይሠራጫል::

**3.3.1.2 በእንሰሳት ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ ኦዲት ኢንስፔክሽን ማካሄድ**

- ✓ 56 በእንስሳት ስጋ እና ተረፈ ስጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ የኦዲት ኢንስፔክሽን ይካሄዳል፡፡

### 3.3.1.3 የስጋና ተረፈ ስጋ አምራች ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት

- ✓ አዲስ ለሚገቡ ኤክስፖርት ቄራወች /ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች ብቃት ከቦታ መጣ ጀምሮ ክትትልና ቅጥጥር በማድረግ ሲያልቁም መመዝገብና የብቃት ማረጋገጫ የመስጠት ሥራ ይከናወናል፡፡
- ✓ በየጊዜው በሚደረግ ኦዲት ኢንስፔክሽን ላይ ተመስርቶ ለ15 ኤክስፖርት ቄራወችን ብቃት ይታደሳል፡፡

### 3.3.1.4 ለኮሜርሽያል የእንሰሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት

ለ71 የማዘጋጃ ቤትና የግል የአገር/ውስጥ ቄራዎችን ከክልሎች ጋር በመሆን መመዝገብና የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

- ✓ ለ35 የእንሰሳት ምርቶችን (ወተት፣ ማር፣ እንቁላል፣ዓሣ) ለሚያቀናብሩና ለሚያደራጁ ድርጅቶች ከክልሎች ጋር በመሆን መመዝገብና የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፣
- ✓ የእንሰሳት ምርቶች (ወተት፣ ማር፣ እንቁላል) ብቃት ማረጋገጫና ማደሻ መስፈርት ማውጣትና መተገበር፣

### 3.3.1.5 በእንስሳት ምርት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት ለ600 ናሙናዎች ይሰራል፡፡

- ✓ 260 የሥጋ ምርት ናሙና ከኤክስፖርት ቄራ ድርጅቶች መሰብሰብ፣ የኬሚካል ቅሪት ምርመራ ማካሄድና ግብረ መልስ መስጠት
- ✓ 260 የሥጋ ምርት ናሙና ከኤክስፖርት ቄራ ድርጅቶች መሰብሰብ፣ የማይክሮባዮሎጂ ጥራት ምርመራ ማካሄድና ምለሽ መስጠት
- ✓ 40 የወተት ምርት ናሙና ከተመረጡ አከባቢዎች መሰብሰብ፣ የፊዚኮ-ኬሚካል ጥራት ምርመራ ማካሄድ
- ✓ 40 የወተት ምርት ናሙና ከተመረጡ አከባቢዎች መሰብሰብ፣ የማይክሮ ባዮሎጅ ጥራት ምርመራ ማካሄድ
- ✓ 40 የማር ምርት ናሙና ከተመረጡ አከባቢዎች መሰብሰብ፣ የጥራትና ኬሚካል ቅሪት ምርመራ ማካሄድ

### 3.2.2 በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች

- ✓ በቁጥር የ390000 ወደ ውጭ የሚላክ የቁም እንሰሳት ጥራቱና ጤንነት ይረጋገጣል፡፡

- ✓ በቁጥር የ546000 ወደ ውጭ የሚላክ የለማ እንቁላል ጤንነቱ እና ደህንነቱ ይረጋገጣል፥
- ✓ ለ450 ቶን ማርና ሰም በኳራንቲን የቁጥጥር ስርአት ውስጥ አልፎ የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት ይሰጣል።
- ✓ ለ 3572450 ያለቀለት ቆዳና ሌጦ የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት ይሰጣል።
- ✓ ለ 689090 ወደ ሀገር የሚገባ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል ጤንነቱ እና ደህንነቱ ይረጋገጣል።
- ✓ ለ275 ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባ የተሸሸለ ዳልጋ ከብት ጤንነቱ እና ደህንነቱ ይረጋገጣል።
- ✓ 12000 ወደ ዐገር ለሚገባ አባላትር ጤንነቱ እና ደህንነቱ የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል።

### 3.2.3 ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት

**ወደ ሀገር ውስጥ ለገባ ወይም ለተመረተ 2,850 ቶን የእንስሳት መድሃኒት ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ይረጋግጣል።**

- ✓ **75 የእንስሳት መድሃኒት ተገምግሞ፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ ይመዘገባል።**
- ✓ **300 የመድሃኒት ናሙዎችን ላይ የጥራት፣ ደህንነት አና ፈዋሽነት የላቦራቶሪ ምርመራ ይካሄዳል።**
- ✓ **375 የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል።**
- ✓ **629 የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ይካሄዳል።**

**በመድኃኒት ምርት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት**

- ✓ **300** የመድኃኒት ምርት ናሙናዎች ላይ የፊዚኮ-ኬሚካል እና ማይክሮባዮሎጂ ጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ይካሄዳል፤
- ✓ **20** የክትባት ምርት ናሙናዎች ላይ የማይክሮባዮሎጂ ጥራት ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ይካሄዳል፣
- ✓ 80 የምግብ ወለድ በሽታ አምጭ ረቂቅ ተዋሲያን ወይም ባክቴሪያ ላይ የጸረ ተዋሲያን መድኃኒት በጀርሞች መላመድ የላቦራቶሪ ምርመራ ይካሄዳል።

### 3.2.4 ጥራትና ደህነነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ

#### 3.3.4.1 **የመኖ ተቋማትና ባለሙያዎች የተሰጠ የብቃት ማረጋገጥ**

**ለ461 የመኖ ተቋማትና ባለሙያዎች** የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፥

- ✓ ለ133 የመኖ ንግድ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ እድሳት ይደጋል፣፡

- ✓ ለ75 አዲስ እና ምትክ የመኖ ንግድ ተቋማት፣/መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ማምረት፣ አስመጪነት፣ ጅምላ ንግድአና ላኪ/የብቃት ማረጋግጫ ይሰጣል፡፡
- ✓ ለ166 የእንሰሳስ መ"ና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የማደስ ስራ ይሠራላል፡፡
- ✓ ለ86 በመኖ ንግድ ተቋማት ለሚሰሩ የመኖ ባለሙያዎች አዲሰና ምትክ ምዝገባና የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣

3.3.4.2 **ጥራትና ደህንነቱ ተጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ መኖ እና የመኖ ግብዓት**

- ✓ **ለ5500 ቶን ወደ መኖ እና የመኖ ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ በአንድ መስኮት አገልግሎት የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡**
- ✓ ለ1321 ቶን መኖና የመኖ ግብዓት ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ በአንድ መስኮት አገልግሎት የመልቀቂያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
- ✓ ለ100 አዳዲስ የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር የሰነድ ፍተሻ በማካሄድ የመመዝገብ ስራ ይከናወናል፣
- ✓ ለ40 እንስሳት መኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ለወጪ ንግድ በሲንግል ዊንዶው የቅድመ ማስወጫ ሰርተፊኬት ይሰጣል፣
- ✓ የብቃት ማረጋገጫ ሳያስፈልጋቸው መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ ለማስገባትና ለማስወጣት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ፈቃድ ይሰጣል፣

3.3.4.3 **የእንሳሰት መኖ እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ማካሄድ**

313 **የእንሳሰት መኖ እና ተቋማት ላይ ኢንስፔክሽን ይካሄዳል፤**

- ✓ በ30 የእንስሳት መኖ አስመጪ ተቋማት ላይ በ 2ዙር ተቋማት ኢንስፔክሽን ይደረጋል፤
- ✓ በ 4 ተቋማት የእንስሳት የመኖ አከፋፋይ ተቋማት ላይ 2ዙር) ኢንስፔክሽን ላየ ይደረጋል፤
- ✓ በ9 የእንስሳት የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች ተቋማት ላይ 2 ዙር ኢንስፔክሽን ይከናወናል፥፡
- ✓ በ59 የእንስሳት የመኖ አምራች ተቋማት ላየ 2 ዙር ኢንስፔክሽን ይከናወናል፡፡
- ✓ የበ21 እንስሳት የመኖ ጥሬ ዕቃ ላኪ ተቋማት ላየ 2ዙር) ኢንስፔክሽን የደረጋል፡፡
- ✓ የእንስሳት መኖ ግብዓት አምራች ድርጅቶችን ወደ ሕጋዊ አሰራር ማስገባት
- ✓ ከመኖ ጥራትና ደህንነት አኳያ ከህዝብ ለሚቀርብ ጥቆማ ምላሽ ይስጣል፡፡
- ✓ 130 የመኖ ናሙና በመሰብሰብ ጥራትና ደህንነቱ የማረጋገጥ ሥራ ይከናወናል፡፡
- ✓ 113651 ቶን የተቀነባበረ የመኖ እና የመኖ ግብዓት ጥራቱና ደህንነቱ የማረጋገጥ ሥራ ይከናወናል፡፡
- ✓ በመኖ ምርት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

- ✓ 130 የእንስሳት መኖ ምርት ናሙናዎች ላይ የፊዚኮ-ኬሚካል እና ማይክሮባዮሎጂ ጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ይከናወናል፡፡

### 3.2.5 ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ አገልግሎት

የተዘረጋ የእንስሳት የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት (ISO/IEC 17025) 100% ለማድረስ ይሰራል፡፡

ለ 20 የእንስሳት የላቦራቶሪ ምርመራ ስነ ዘዴዎች እውቅና/አክሪዲቴሽን ያገኛሉ፡፡

- 84 ስታንደርድ የአሰራር ፕሮስጀሮችን እና የላቦራቶሪ ምርመራ ስነ ዘዴዎችን ማዘጋጀትና ነባሮችን የመከለስ ስራ ይከናወናል፡፡
- 14 የምርመራ ስነ ዘዴዎች የትክክለኝነት ማረጋገጫ ቫሊዴሽን ወይም ቬርፊኬሽን እና ተጓደኝ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡
- 31 የላቦራቶሪ መሳሪያዎች የቅድመ ብልሽት መከላከልና የብልሽት ጥገና ሥራ ይከናወናል፡፡
- 245 የላቦራቶሪ መሳሪያዎች የልኬት ማረጋገጫ ወይም ካሊብሬሽንና የኮምፕሊያንስ ቨሪፊኬሽን እንዲሰራላቸው ይደረጋል፡፡
- 20 የብቃት ማረጋገጫ ወይም የፕሮፌሽንሲ መለኪያ የላቦራቶሪ ምርመራ ሥራ ይከናወናል፡፡
- የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ሥርዓት ትግበራ የውስጥ ኦዲት ሥራ ማከናወንና በኦዲት ግኝት ላይ ማስተካከያ ይደረጋል፡፡
- የጥራት ማኔጅመንት ሥርዓት ትግበራ የማኔጅመንት ሪቪው/ግምገማ ማካሄድና የማሻሻያ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡
- ተጨማሪ እውቅና ለማግኘት የሚረዱ ሰነዶችን ማደረጀትና የሶስተኛ ወገን የእውቅና ጥያቄ ለኢትዮጵያ አክሪድቴሽን አገልግሎት ይቀርባል፡፡
- ለኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት በሰነድ ግምገማ ወቅት ለሚጠይቃቸው ተጨማሪ የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን፣ አስፈላጊ ሰነዶችን ማቅረብ እና ምላሽ ይሰጣል፡፡
- የእውቅና ሰጪ ተቋም ባለሙያዎች በማዕከሉ ተገኝተው ለሚያካሂዱ የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትግበራ የአካል ምልከታና የኦዲት ሥራ ፕሮግራም ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና የማስተባበር ስራዎች ይከናወናሉ፡፡
- የጥራት ማኔጅመንት ሥርዓት ትግበራ በዕውቅና ሰጪ ተቋም የውጭ ኦዲት ሥራ እንዲካሄድ ማድረግና በውጭ ኦዲት ግኝት ላይ የማስተካከያ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡
- የአክሬዲቴሽን/እውቅና ሰርተፊኬት ርክክብ ፕሮግራም ማዘጋጀት እና በሚዲያ የማስተዋወቅ ስራ ይከናወናል፡፡

## 4 ተቋማዊ የመፈፀም አቅም፣ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምና አገልግሎት አሰጣጥ እና የህግ ማዕቀፎች

### 4.1 የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማጠናከር

- የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ሬጉላቶሪ ስርዓትን ለማጠናከር እና ተግባራዊ ለማድረግ ለ15 ባሙያዎች የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት
- የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ሬጉላቶሪ ስራዎችን በማዕከላትና ጣቢያ 4 ዙር ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ተቋማትን 3 መረጃ ሰነድ ማሰባሰብንና ማደራጀት
- ወደ ሀገር የሚገቡ የግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያዎች 1 መረጃ ማደራጀት
- የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ሬጉላቶሪ ስራዎችን ለማሳለጥ የዳሰሳ 3 ጥናት ማካሄድ
- በፀረ ተባይና ማዳበሪያ ዙሪያ ለማዕከላት እና ለጣቢያ ሰራተኞች የተለያዩ ቴክኒካል ስልጠና በሀገር ውስጥና በውጭ ሃገር ይሰጣል
- የተገልጋዮችና የባለድርሻ አካላት የጋራ የምክክር መድረክ ማዘጋጀት
- ለክልል ተቆጣጣሪ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት
- ለ 80 ባለሙያዎች በጥራት ማኔጅመንት ስርዓት ትገበራ፣የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራት ምርመራ እና ተያያዥ ቴክኒካል ሥራዎች ላይ ሥልጠና መስጠት.
- ለ 80 የተቋሙ ሠራተኞች የሥራ ላይ ደህንነት አጠባበቅ ሥልጠና መስጠት.
- ለ 20 ባለሙያዎች የላቦራቶሪ መሳሪያዎች አጠቃቀምና መለስተኛ ጥገና ሥልጠና መስጠት.
- ለ 80 የአርብቶ አደር አከባቢ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች በእንስሳት መድኃኒት ክትባት ጥራት ቁጥጥርና አጠቃቀም፣የእንስሳት ተዋጽኦ ጥራት ቁጥጥርና ቅኝት ላይ ሥልጠና መስጠት.
- ለ 40 የክልል የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች በጸረ-ተዋሲያን በጀርሞች መለመድ የላቦራቶሪ ምርመራ ግኝትና የሥጋት ቅነሳ ዘዴን በተመለከተ የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥልጠና መስጠት፤

### 4.2 ተግባራዊ የተደረገ የህግ ማዕቀፍ

- 2 የግብርና ሜካናይዜሽን የአሰራር ስርዓት እና የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት
- 1 የግብርና ምርምር የአሰራር ስርዓት እና የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት
- 1 የግብርና ኤክስቴንሽን የአሰራር ስርዓት እና የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት
- 5 የግብርና ማሽነሪዎች ብሔራዊ ስታንዳርዶችን መከለስ
- 1 የግብርና ኤክስቴንሽን አተገባበር ሬጉላተሪ ማንዋል ማዘጋጀት

- 1 የፀረ ተባይና ማዳበሪያ  የህግ ማዕቀፍ  ,የደረጃ እና የፕሮቶኮሎች  ክፍተት ለመለየት የሚያስችል ጥናት ማድረግ
- 2 የፀረ ተባይና ማዳበሪያ ለአዳዲስ የህግ ማዕቀፍ,ደረጃ እና ፕሮቶኮሎች  .የመጀመሪያ ረቂቅ ማዘጋጀት
- 4 የፀረ ተባይና ማዳበሪያ በዝግጅት ሂደት ላይ ያሉ የህግ ማዕቀፎችን ,ደረጃ እና ፕሮቶኮሎች ረቂቅ የማጠናቀቅ ስራ መስራት
- የእንሰሳት ውጤቶች ጤንነትና ደህንነት ቁጥጥር ረቂቅ -----ደንብ ማዘጋጀት
- የሥጋ ምርመራና ሃይጂን ረቂቅ ----- ደንብ ማዘጋጀት
- የእንሰሳት ውጤቶች የኂልዮሽ ክትትል ሥርዓት------ ረቂቅ መመሪያ
- የሥጋና የሌሎች የእንሰሳት ውጤቶች ምርመራ ረቂቅ መመሪያዎች

**4.3 የስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ሪፖርት ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ-መልስን ማሻሻል**

- የተሻሻል የዕቅድ፣ክትትልና ግምገማና የመረጃ አስተዳደር ስርዓት ይገነባል
- በበጀት ዓመቱ ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ዕቅድና 4 ሪፖርት ሰነድ ይዘጋጃል፡፡
- የክትትልና ግምገማ ስርዓት የመዘርጋትና የማሻሻል ስራዎች ይከናወናሉ፡፡
- የኘሮግራም በጀት እቅድ ዝግጅትና ክንውኑን የመከታተል ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

**4.4 የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል**

- ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት ማካሄድ
- ለአመራር እና ለሰራተኞች የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ማሳደግ
- የሰራተኛ እርካታን በማሳደግ ፍልሰትን መቀነስ

4.5 የፋይናንስና ግዥና  አስተዳደር

- የተመደበ በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል
- ነቀፌታ ያለበትን የኦዲት ግኝት መቀነስ
- የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ክፍያን ድርሻ ማሳደግ
- የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ድርሻ ማሳደግ

4.6 መሰረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት የደንበኞችን እርካታ ማሻሻል

- የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ
- ኤሌክትሮኒክስ የንብረት ቁጥጥር ሥርዓት በአግባቡ መተግበር

4.7 የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ለውጤታማነትን ማሻሻል

- መረጃ ቋት ማደራጀት
- በተቋሙ ወረቀት አልባ አሰራርን የመተግበር ደረጃን ማሻሻል

4.8 ተቋማዊ የሪፎርም ሥርዓት በመጠቀም የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ

- አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ
- መጠይቆችን በማዘጋጀት የተገልጋዮች እርካታ ደሰሳ ጥናት ማካሄድ፣መረጃውን መተንተንና ከተገልጋዮች በሚሰጥ ግብረ መልስ መሰረት የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ እንዲሻሻል ማድረግ፤
- ከተገልጋዮች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የቅሬታ አፈታት አሰራር ሥርዓት መሰረት ማጣራት እና ተገቢውን ምላሽ መሥጠት፤

4.9 አጋርነትና ህዝብ ግንኙነት

በ2016 ከተደረገው ጥረት በላቀ ሁኔታ ተጠናክሮና ተሻሽሎ ይቀጥላል፡፡

## 4.10 ክትትልና ግምገማ

ባለስልጣኑ ለሚያከናወናቸው የቁጠጥር ስራዎች በተለያየ ደረጃ የክትትል ድጋፍና ግምገማ ስራዎችን የሚያከናው ሲሆን ይህም በዋናው መ/ቤትና በማዕከላት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶቾ ጭምር የሚከናወን ሆኖ በሁሉም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች ባሉ ማዕከላት የክትትልና ድጋፍ አገልግሎት እንዲሁም በአራቱም ሩብ አመታት የአፈጻጸም ግምገማ ሥራዎች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

## ማጠቃለያ /ቀጣይና ዋና  የትኩረት አቅጣጫዎች

ባለስልጣኑ ከተሰጠው ተልዕኮ ሳይወጣና ያስቀመጠውን  ስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት በማድረግ ቀጣዮቹ ጉዳዮች ላይ በትኩረት ይሠራል፡፡

- ✓ መንግስት ያስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በማድረግ በምግብ እራስን በመቻል ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሥራው ቁልፍ ሚና ይጫወታል በመሆኑም የግብርና ግብዓቶትና ምርቶችና አገልሎቶችን ጥራትና ደህነነትን ለማረጋገጥ ጠንካራ የቁጥጥር ሥራ ማካሄድ፣
- ✓ በአካባቢና በዜጐች ላይ የሚደርሰውን ብክለትና የጤና ችግሮች ለመቅረፍ በጥናት ላይየተመሠረተ ቁጥጥር በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃወች መውሰድ፣
- ✓ ወደ ውጭ የማላኩ ምርቶዎችንን በዓለም ገበያ ጥራትና ደህነታቸው ተጠብቀው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ጠንካራ የበሽታና የተባይ ቁጥጥር ማድረግ፣
- ✓ በተለይም በኤክስፖርት ምርቶች ላይ የሚከሰቱ የፀረ ተባይ ቅሬታወች አፍላቶክሲን የመሳሰሉትን የመከላከል ሥራ በተጠናከረ ሁኔታ መሥራት፣
- ✓ የሰው ኃይል ብቃት መገንባት በተለይም የሙያ ብቃት የሚያሳድግ ሥልጠዎችና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መሠራት፣
- ✓ ሁሉም አገልግሎቶች ወደ ዲጂታላይዜሽን ማሸጋገር፣

- ✓ ተቋማችን የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲግረው ማድረግ ፣ የፀደቁ የህግ ማዕቀፎችን ሥራ ላይ ማዋል እንዲሁም ያልፀደቁ የህግ ማዕቀፎች ማፀደቅና የማያስፈልጉ አዳዲስ ህጉች በማጥናት ማዘጋጀት፣
- ✓ በተጠናከረ ሁኔታ ሀብት ማፈላለግ ሥራ መሥራት ትኩረት የሚሹ ጉዳዩች ናቸው፡፡

| **የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣንየ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቸ** | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾቸ** | መለኪያ | መነሻ የ2016 አፈጻጸም | የ2017 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| **ንዑስ ፕሮግራም ፡-በዕጽዋትና ከዕጸጽዋት ጋር በተገናኙ ግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ማጠናከር** | | | | | | | |
| **ፍቱንነቱ፣ደህንነቱ እና ጥራቱ የተረጋገጠ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ** | | | | | | | |
| ፍቱንነቱ፣ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የፀረ ተባይ | ቶን | 78,343.00 | 111,437.00 | 17,850 | 17,850 | 20018 | 20020 |
| ጥራቱ የተረጋገጠ የአፈር ማዳበሪያ | ቶን | 2,510,360.00 | 2,339,971.00 | 562,779.00 | 562,779.00 | 762,779.00 | 612,779.00 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 198 | 195.00 | 150 | 15 | 15 | 15 |
| በአከባቢ እና በጤና ላይ የሚደርሰውን ስጋቶችን በጥናት መቀነስ | በቁጥር | 1 | 2 | | 1 | | 1 |
| **ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ የቀረቡ የዕጽዋት ምርቶች** | | | | | | | |
| ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ዕጽዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች | ሜ/ቶን | 87,531.00 | 860,000 | 215,000 | 215,000.00 | 215,000.00 | 215,000.00 |
| ጥራትና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕፅዋት እና የዕፅዋት ዉጤቶች | ሜ/ቶን | 39,643.00 | 60,000 | 15,000.00 | 15,000.00 | 15,000.00 | 15,000.00 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 638 | 230 | 57 | 58 | 57.00 | 58.00 |
| **የዕጽዋት ዝርያ ጥበቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር** | | | | | | | |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣንየ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | መለኪያ | መነሻ የ2016 አፈጻጸም | የ2017 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| በምርምር ቀርበው የተገመገሙ ዕጩ የዕፅዋት ዝርያዎች | ቁጥር | 164 | 120 | 20 | 60 | 30 | 10 |
| ጥራትና ዉጤታማነታቸው ተረጋግጦ የተመዘገቡና የተለቀቁ የዕፅዋት ዝርያዎች | ቁጥር | 75 | 78 | | | 60 | 18 |
| በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ የአገር ውስጥ ዘር | ኩንታል | 829,197 | 1,527,905 | | | 1,145,928 | 381,977 |
| በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ ከውጭ አገር የገባ ዘር መጠን ውስጥ ለላብራቶሪ የቀረበ የናሙና ብዛት | ቁጥር | 303 | 250 | 50 | 70 | 70 | 60 |
| በቁጥጥር ሰንሰለት አልፎ ጥራቱ የተረጋገጠ ከውጭ አገር የገባ ዘር | ኩንታል | 617, 640 | 509,603 | 101,920 | 142,688 | 142,688 | 122,304 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ድርጅቶች | ቁጥር | 30 | 30 | 5 | 10 | 10 | 5 |
| **ውጤታማነቱ፣ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ** | | | | | | | |
| ውጤታማነቱ ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ የግብርና ምርምር፣ ኤክስቴንሽንና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ | በቁጥር | | 20 | | | 10 | 10 |
| በኢንስፔክሽን ብቃታቸው የተረጋገጠ የምርምር፣ የኤክስቴሽንና የመካናይዘሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት | በቁጥር | | 30 | | | 15 | 15 |
| **ንዑስ ፕሮግራም፦ የእንስሳትና ከእንስሳት ጋር የተገናኙ የግብዓቶች፣ ምርቶች፣ ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ቁጥጥር ማጠናከር** | | | | | | | |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቾ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁልፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ የ2016 አፈጻጸም | የ2017 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| **የእንስሳት ምርቶችን ጤንነት ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ** | | | | | | | |
| ደህንነቱ ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ስጋና ተረፈ ሥጋ | በቶን | 18,647.53 | 15,000 | 3,750 | 3,750 | 3,750 | 3,750 |
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የስጋና ተረፈ ስጋ አምራች ተቋማት | በቁጥር | 12 | 15 | | 15 | | |
| ጥራቱና ደህንነቱ በላቦራቶሪ ፍተሻ የተረጋገጠ የእንስሳት ምርት ናሙናዎች | ቁጥር | 480 | 600 | 120 | 180 | 180 | 120 |
| ለኮመርሻል የእንስሳት ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ | በቁጥር | 55 | 71 | | 35 | | 36 |
| በእንስሳት ሥጋ እና ተረፈ ሥጋ ማቀነባበሪያ ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | ቁጥር | 56 | 56 | 14 | 14 | 14.00 | 14.00 |
| **በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች** | | | | | | | |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ የቁም እንስሳት | ቁጥር | 256,809 | 390,000 | 95,000 | 100,000 | 95,000 | 100,000 |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ የለማ እንቁላል | ቁጥር | 4,535,602 | 546,000 | 136,000 | 136,000 | 137,000 | 137,000 |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ሰምና ማር | ቶን | 145 | 450 | 110 | 110 | 120 | 110 |
| ጥራቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ የተላከ ቆዳና ሌጦ | ቁጥር | 3,060,464 | 3,572,450 | 890,000 | 897,450 | 895,000 | 890,000 |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣንየ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቾ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | መለኪያ | መነሻ የ2016 አፈጻጸም | የ2017 ዕቅድ | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል | ቁጥር | 889,637 | 689,090 | 172,000 | 173,000 | 172,000 | 172,000 |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ የተሻሻለ ዳልጋ ከብት | ቁጥር | 120 | 275 | 70 | 68 | 67 | 70 |
| ጥራቱና ጤንነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር የገባ አባላዘር | ዶዝ | 59,872 | 12,000 | 3,000 | 3,000 | 3,000 | 3,000 |
| **ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት** | | | | | | | |
| ጥራት፣ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ የእንስሳት መድሃኒት | በቶን | 3043 | 2,850 | 712.5 | 712.5 | 712.5 | 712.5 |
| ተገምግሞ፣ በኢንስፔክሽን ስርዓትና በላቦራቶሪ ምርመራ ተረጋግጦ የተመዘገበ የእንስሳት መድሃኒት | በቁጥር | 94 | 75 | 18 | 19 | 19 | 19 |
| የመድሃኒት ናሙዎችን ላይ የተካሄደ የጥራት፣ ደህንነት እና ፈዋሽነት የላቦራቶሪ ምርመራ | በቁጥር | 305 | 300 | 75 | 75 | 75 | 75 |
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት | በቁጥር | 313 | 375 | 93 | 94 | 94 | 94 |
| የእንስሳት መድሃኒት እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 536 | 629 | 157 | 157 | 157 | 158 |
| **ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መኖ** | | | | | | | |

| የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣንየ2017 ዕቅድ በቁልፍ አመልካቾ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ አመልካቾች** | **መለኪያ** | **መነሻ የ2016 አፈጻጸም** | **የ2017 ዕቅድ** | **1ኛ ሩብ ዓመት** | **2ኛ ሩብ ዓመት** | **3ኛ ሩብ ዓመት** | **4ኛ ሩብ ዓመት** |
| የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኙ መኖ አምራች፣ ላኪ፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት | በቁጥር | 310 | 461 | 230 | 122 | 70 | 39 |
| በእንስሳት መኖ እና ተቋማት ላይ የተካሄደ ኢንስፔክሽን | በቁጥር | 247 | 313 | 72 | 83 | 86 | 72 |
| ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም የተመረተ መኖ እና የመኖ ግብዓት | ቶን | 6273.218 | 5,500 | 1375 | 1375 | 1375 | 1375 |
| የመኖ እና የመኖ ጥሬ ግብዓት ናሙናዎች ላይ የተካሄደ የጥራት እና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ | ቁጥር | 8 | 130 | 30 | 40 | 40 | 20 |
| ጥራቱና ደህንቱ ተረጋግጦ የተመረተ የተቀነባበረ መኖ እና የመኖ ግብዓት | ቶን | --- | 113651 | 28401 | 28415 | 28415 | 28420 |
| **ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የዕጽዋት ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ አገልግሎት** | | | | | | | |
| የተዘረጋ የእንስሳት የላቦራቶሪ ጥራት ማኔጅመንት ስርዓት (ISO/IEC 17025) ትግበራ | ቁጥር | 16 | 14 | | | | 14 |
| እውቅና/አክሪዲቴሽን የተገኘባቸው የእንስሳትና የዕጽዋት የላቦራቶሪ ምርመራ ስነ ዘዴዎች | ቁጥር | | 20 | | | | 20 |